# ምእራፍ አራት

## መድረክና የመድረክ ዝግጅት

### 4.1. መድረክ

ቀደም ባሉት ጊዜያት ተውኔቶች በመንገድ ላይ፣ በሜዳ ላይ፣ ገባያ ላይ፣ወዘተ. ይቀርቡ እንደነበር የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት እንደ አሁኑ ዘመን ለተውኔት ማሳያ ተብለው ለራሱ የተዘጋጁ መድረኮች ባለመኖራቸው ነበር። በአለንበት ዘመን ግን ሶስት አይነት መድረኮች ስራ ላይ ይውላሉ። እነዚህም፣ ትይዩ (ፊት ለፊት) መድረክ፣ ዙሪያ ገብ (ክብ)መድረክና ግፊታዊ (ሶስትዮሽ) መደረክ በመባል ይታወቃሉ።

**ትይዩ መድረክ** (End stage):-

ይህ አይነቱ መድረክ ከተውኔቱ ታዳሚ መቀመጫ ፊት ለፊት ከፍ ብሎ የሚገነባ የመተወኛ ቦታ ነው። ይኸውም ተዋንያኑ ከታዳሚው ፊት ለፊት በመቅረብ የሚተውኑበት ቦታ ነው። ይህ አይነቱ መድረክ ተዋንያኑና ድርጊታቸው ከፍ ብለውና ገዝፈው ለተመልካች እንዲታዩ ለማድረግ ያግዛል።

ይህ አይነቱ መድረክ ከሌሎቹ የበለጠ እውነታዊነት ይታይበታል። የሚቀርበው ተውኔት ልዩ ልዩ ገቢሮችና

ትእይንቶች ሲቀየሩ የሚዘጋና የሚከፈት መጋረጃ መኖሩም ለእውነታዊነቱ አስተዋጽኦ ያበረክትለታል። ይሁን እንጅ እንዲህ አይነቱ መድረክ የራሱ ድክመትም አለበት። ይኸውም በተመልካችና በገጸባህሪያቱ መካከል መራራቅን ስለሚፈጥር ለሁሉም የተውኔት አጻጻፍ ስልቶች አመች ላይሆን ይችላል።

**ዙሪያ ገብ መድረክ** (Arena stage)፡-
ይህ አይነቱ መድረክ ደግሞ እንደ እግር ኳስ ሜዳና መሰል ቦታዎች በታዳሚው ዙሪያውን የተከበበ የመተወኛ ስፍራ ነው። ይኸውም ተዋንያኑ መካከል ላይ ሆነው ታዳሚው ዙሪያውን በመሆን ተውኔቱ የሚከወንበት መድረክ ነው።

ይህ አይነቱ መድረክ ሲዘጋጅ ከተመልካቹ መቀመጫ መሀል ዝቅ ብሎ ነው። ይህ ደግሞ በተመልካችና በተዋንያን መካከል መቀራረብን ይፈጥራል። በዚህም የተነሳ ተመልካቹ እያንዳንዱን ነገር ተመልክቶ ለማረጋገጥ እድሉ ከፍተኛ ነው። የዙሪያ ገብ (ክብ) መድረክ ጉዳቱ ተዋንያኑ ተቀምጠው ተራቸውን የሚጠባበቁበትና ለመተወኛ ስፍራው ቀረቤታ ያለው ክፍል አለመኖሩ ነው። ተዋንያኑ ተራቸው ደርሶ ሲገቡም ሆነ ተራቸውን ጨርሰው ሲወጡ ተመልካቹን አቋርጠው ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ይገደዳሉ።

**ግፊታዊ** (**ሶስትዮሽ**) **መድረክ** (Thrust stage)፡-

ይህ አይነቱ የመድረክ መልክ ልክ እንደዙሪያ ገብ መድረክ ሆኖ ይገነባል። ከዚያም ሶስት አራተኛውን እጅ ለተመልካች በመተው ቀሪ አንድ አራተኛው የመድረኩ ክፍል ደግሞ ለተዋንያኑ መቆሚያ የሚተውበት ነው። ይኸውም ታዳሚው
ከተዋንያኑ ጀርባ ያለውን ቦታ ብቻ በመተው በሶስት ጎን ማለትም በፊት ለፊት፣ በግራና በቀኝ ተመልካቹ የሚቀመጥበት መድረክ ነው።

የዚህ አይነቱ መድረክ ጠቀሜታው በተመልካችና በተዋንያን መካከል ቅርርብ ይፈጥራል። ከዚህም በተጨማሪ ከትእይንት ወደ ትእይንት እና ከገቢር ወደገቢር ለሚደረገው ሽግግር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። ይሁን እንጅ ይህ የመድረክ መልክ በቂ ልምድ ያካበቱ አዘጋጆችንና የመድረክ ንድፍ ባለሙያዎችን ስለሚፈልግ አስቸጋሪነት ይስተዋልበታል።

## 4.2. የመድረክ ዝግጅት

ተውኔት የተደራሲን ቀልብ ማርኮ መያዝ ይችል ዘንድ በመድረኩ አካባቢ የሚፈጠረው ጥበባዊ ምትሀት ላቅ ብሎ መገኘት ይኖርበታል። ጥበባዊ ምትሀቱ ከፍ ይል ዘንድም ዋነኛው ጉዳይ የአውድ መገለጫ (spectacle) ነው። ይህ የአውድ መገለጫ የብዙ ባለሙያዎችን ትብብር የሚጠይቅ ነው። እነዚህም በመድረክ አሳሳል ሂደት በተግባር ላይ የሚውሉ የጣራ፣ የግድግዳ፣ የወለል

ቁሳቁሶችና የመደረኩ ዙሪያ ገብ መልኮች፣ አልባሳት፣ የገጸባህሪያት አካላዊ እንቅስቃሴዎችን የሚከስቱ ናቸው።
የመድረኩ መከሰቻ አውድ በመድረኩ ላይ ጎልቶ ይታይ ዘንድ ብሎም የተውኔቱን ጥበባዊ ፋይዳ ከፍ ያደርገው ዘንድ የመድረክ ባለሙያዎቹ ድርሻ ቁልፍ ጉዳይ ነው። እነዚህንም ቀጥለን እንመልከት።

❖ ጸሃፌ ተውኔት፡-

ጸሀፌ ተውኔት የተውኔት ድርሰቱን የሚጽፍ ባለሙያ ነው። ይህ ባለሙያ የተውኔቱን ታሪክ ዝም ብሎ የሚዘረዝር ሳይሆን ገጸባህሪያቱ ምን እንደሚያደርጉ፣ እንቅስቃሴያቸው ምን መምሰል እንዳለበት፣ የመብራት ሁኔታን፣ የአካል እንቅስቃሴን፣ በአካባቢው የሚያስፈልጉ ነገሮችን፣ ወዘተ. ጥቆማ በመስጠት ይጽፋል።

❖ መራሄ ተውኔት (አዘጋጅ)፡-

ጸሀፌ ተውኔቱ የተጠበበበትን ኪነታዊ ስራ ለዳግማዊ ልደቱ ለማብቃት ወደ ተግባር ኪናዊ ክንዋኔ ለውጦ ከተደራሲያን ፊት ለማቅረብ፣ ጠቅላላ ሂደቱን የሚመራ ባለሙያ ነው። ይህ ባለሙያ ድርጊቶችን፣ መድረኩን፣ አልባሳቱን፣ ወዘተ. የሚመራ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለተውኔቱ አስፈላጊ የሆኑ ድርጊያዎችን፣ ውዝዋዜ፣ ቋንቋና የመሳሰሉትን አንድምታ የሚፈታ ነው።

መራሂ ተውኔት አንድን ተውኔት ወደ መድረክ ከማውጣቱ በፊት የተውኔት ጽሁፉን አንድምታ መገንዘብ አለበት። ይህም ማለት የተውኔቱን ጠቃሚና መጥፎ ጎን በመለየት ሂሳዊ እይታን ማዳበር የመጀመሪያ ተግባሩ መሆን አለበት። ከዚህ አይነቱ ፍተሻ በኋላ መድረኩ ተገቢና ማራኪ በመሆን የታዳሚን ልብ እንዲረታ ለማድረግ ሊጠቀምባቸው የሚገባቸውን የድምጽና የብርሀን ግብአቶች ማሰላሰል አለበት። ይኸውም በትእይንቶች መዳረሻ የሚለቀቀውን ብርሀን፣ የተውኔቱን ማጀቢያ ሙዚቃ፣ ሊለበሱ የሚችሉ አልባሳት፣ ሊደረግ የሚገባውን አካላዊ እንቅስቃሴና መሰል ሁኔታዎችን ይመረምራል። ለዚህም ተስማሚ የሆኑ ባለሙያዎችን በመምረጥ ለተግባር ያሰልፋል።

❖ ተዋንያን፡-

በጸሀፊ ተውኔቱ ተጽፎ በመራሂ ተውኔቱ የተቀናበረው ስራ በመድረክ ላይ እውን የሚሆነው በእነዚህ ባለሙያዎች ነው። ተዋንያኑ በተውኔት ጽሁፉ ውስጥ ያሉትን ገጸባህሪያት ወክለው በመድረክ የሚቀርቡ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ባለሙያዎች አደራቸውን የሚወጡት ተፈጥሯዊ ሰብዕናቸውንና አካላዊ መልካቸውን በመሻርና ለጊዜውም ቢሆን በገጸባህሪያቱ አኳኋን በመቅረጽ ነው።

❖ የመብራት ባለሙያ፡-

የመብራት ባለሙያ ከአዘጋጁ ጋር በተነጋገሩት መሰረት ተውኔቱ በመድረክ ላይ ሲውል አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ የመብራት አገልግሎትን የሚሰጥ ባለሙያ ነው። ለምሳሌ መምሸት መንጋትን። የመብረቅ ብልጭታን፣... ለማመልከት ሲፈለግ የዚህ ባለሙያ እገዛ የግድ ነው።

- **የአልባሳት ባለሙያ፡-**

ጸሀፌ ተውኔቱ እንደጻፈው፣ አዘጋጁ እንደሚፈልገው ገጸባህሪያቱ በተለያየ ጊዜ የሚለብሱትን ልብስ የሚያዘጋጅ ባለሙያ ነው።

- **የሜካፕ ባለሙያ፡-**

ተዋንያኑ በተለያየ ጊዜ መስለው ( ሆነው) መቅረብ የሚገባቸውን ለመምሰል የሚቀባቡ ነገሮችን እንዲያደርጉ የሚያግዝ ባለሙያ ነው።

- **የድምጽ ባለሙያ፡-**

በተውኔቱ ውስጥ ለሚፈለግ ድምጽ አቀናባሪ ባለሙያ ነው። አስፈላጊና ከተዋንያኑ የማይወጣ ማናኛውንም ድምጽ በመድረካ ላይ እንዲሰማ የሚያደርግ ነው። ለምሳሌ ሙዚቃ ሲፈለግ የሚለቀቀው በዚህ ባለሙያ ከመድረክ በስተጀርባ ነው። በመሆኑም የዚህ ባለሙያ የስራ ድርሻ ትክክለኛ ድምጽን የመምረጥ፣ በሰአቱ የመልቀቅና የማቆም ተግባራትን ማከናወን ነው።

❖ የመድረክ ቁሳቁስ፡-

ለተውኔቱ የሚያስፈልጉ ማንኛውንም አይነት ቁሳቁሶች ይመለከታል። እነዚህ ቁሳቁሶች እንደ ተውኔቱ ሊለያዩ የሚችሉ፣ ተዋንያኑ የሚጠቀሙባቸው፣ መቼትን ለመግለጽ የሚያገለግሉ፣ መድረክን በገቢር ለመከፈል የምንጠቀምባቸውና መሰል ለተውኔቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሁሉ ያጠቃልላል።

በአጠቃላይ የመድረክ ዝግጅቱ የተዋጣና ያማረ ሊሆን የሚችለው ከላይ ያነሳናቸውን በአንድነት አዋህዶና አቀናጅቶ መጠቀም ሲቻል ነው። ይህን የመወጣቱ ከፍተኛ ድርሻ ደግሞ በመራሄ ተውኔቱ ትከሻ ላይ የሚወድቅ ነው የሚሆነው። ያ ሲሆን ነው ተውኔቱ ከታዳሚው ዘንድ ደርሶ የታለመውን ግብ ሊመታ የሚችለው።